የሰ/መ/ቁ. 39808

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ናዝሬት ሳሙና ፋብሪካ

**ተጠሪ፡-** ዘውዴ ኃ/ማሪያም /አቶ/

መዝገቡን መርምረን የሚተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተደረገውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ስራዬን በገዛ ፈቅዴ ለቅቄ ስራ ያቋረጥኩ ስለሆነ በሕጉ መሰረት የስንብት ክፍያና የአገልግሎት ክፍያ ይከፈለኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ በፋብሪካው ውስጥ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ያገለገለና በፈቃዱ ስራውን የለቀቀ በመሆኑ እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አገልግሎት አበል ለእድሜልክ ማግኘት ይችላል፡፡ ስለዚህ የአገልግሎት ክፍያ የማግኘት መብት የለውም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስሰተናገደው ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኂላ፣የአመልካች ክርክር በመቀበል ተጠሪ የጠየቀውን ክፍያ ማግኘት አይችልም በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ባለመቀረቡ ክርክሩ የተሰማው እሱ በሌለበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ የጡረታ የተጠበቀ ቢሆንም፣የስንብት ክፍያም ይከፈለው በሚል የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው ተጠሪ በራሱ ፈቃድ ስራውን በመልቀቁ ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ ወደ ክስ ያመራውም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39 መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ ለመክፈል አመልካች ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ ነው፡፡ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያው መክፈል የለበኝም የሚለው ተጠሪ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ያገለገለ በመሆኑ በጡረታው ሕግ መሰረት የጡረታ አገልግሎት አበል የማግኘት መብት አለው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ነው፡፡ በእርግጥም የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለውና በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ እድሜ ደርሶ ከስራ የተገለለ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2)(ሰ) ተመልክቶአል፡፡ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥብት የስራ ስንበት ክፍያ የሚፈጸምለት ሊቋቋመው የማይችል ድንገተኛ የገንዘብ ችግር እንዳይገጥመው ነው፡፡ ይህ ከሕጉ በስተጀርባ ያለው አስተሳስብ ወይም ምክንያት ሲሆን በሕጉ

እንደተመለከተው ሰራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን የጡረታ መብት ካለው ግን የስራ ውሉ ቢቋረጥም፤ ገንዘብ ማግኘቱን ስለሚቀጥል (ስለቀጠለ) የስራ ስንብት ክፍያው አይከፈለውም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የስራ ውሉን ያቋረጠው በፋብሪካው ውስጥ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ካገለገለ በኋላ ነው ቢባልም፤በጡረታ ሕጉ መሰረት የጡረታ እድሜ ላይ ስለመድረሱና የጡረታ አበል የሚያገኝ ለመሆኑ አመልካች አላስረዳም፡፡ ተጠሪ የስራ ውሉን እንዳቋረጠ የጡረታ አበል ማግኘቱን ይቀጥላል የሚል ክርክርም ሆነ ማስረጃ ከሌለ ደግሞ ለስራ ስንብት መከፈል መሰረት የሆነውን በሕጉ በስተጀርባ ያለውን ምክንያት መሰረት በማድረግ የስራ ስንብቱን ክፍያ ማስከፈል የግድ ይሆናል፡፡ ሕጉ በዚህ መልክ ካልተተረጐመም ሰራተኛው ለድንገተኛ የገንዘብ ችግር ማጋለጥ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ለወደፊት የጡረታ አበል ያገኛል በሚል መነሻነት አመልካች ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል የስራ ስንብት ክፍያው እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ይህ ውሳኔ በበኩላችንም የምንደግፈው ነው፡፡ ውሳኔውን የደገፍነው ሕጉ ከላይ በተገለጸም አይነት መተርጐም ያለበት መሆኑን ስለምናምን ነው፡፡ ስለዚህም የከፍተኛው ፍ/ቤት  የሕጉን ትርጉም በሚፈለገው መጠን ባያስቀምጥም፣የደረሰበት መደምደሚያ ግን ትክክል ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06414 ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. ተጠሪ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ክፍያው ይፈጸምለት ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

## <u>ት እ ዛ ዝ</u>

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ